United Ethiopian Muslims Peaceful Movement Support Group
የኢትዮጵያ ሙስሊሞች ሰላማዊ ንቅናቄ ደጋፊዎች ሕብረት
4324 Georgia Avenue NW – Washington, DC 20011 uempmsg@gmail.com

November 2, 2016

ከኢትዮጵያውያን ሙስሊሞች ሰላማዊ ንቅናቄ ደጋፊዎች ሕብረት ስለ አዲሱ ጥምረት
“የኢትዮጵያውያን አገራዊ ንቅናቄ” የተሰጠ ወቅታዊ መግለጫ

# አንድነት ድል ነው!

ኢትዮጵያ ሃገራችን በዘረኛው ወያኔ ድንብርብሩ በወጣ አመራር መቀመቅ ለመግባት የቁልቁለት መንገድ ከጀመረች 25 ዓመታት አስቆጥራለች። ገና ከጅምሩ ወያኔ ለሃገራችንና ለሕዝቧ እንደማይበጅ የፍንጭ እጥረት አልነበረም። ሌሎቹን ፍንጮች ሳንዘረዝር፣ የትግራይ ሕዝብ ነፃ አውጪ ግንባር የተሰኘ ድርጅት ሁሉን አካታችና ጠቃሚ የሆነ ሃገራዊ  አጀንዳ ይኖረው ይሆናል ብሎ በማመን ሲጀመር ልብን ከፍቶ መስጠት የዋህነት ብቻ ሳይሆን ለሃገርና ለመጪው ትውልድ ያለንን ሃላፊነት መዘንጋትም ጭምር ስለሆነ በታሪክ ከተወቃሽነት አንድንም። ስለሆነም ለ25 ዓመታት ወያኔ ላጠፋው የንፁሃን ሕይወት፣ በስር ቤት ላንገላታቸው ወገኖቻችን፣ ካገር ለተሰደዱት፣ በኮንቴይነር ውስጥ ታፍነው ላለቁት፣ በደቡብ አፍሪካ በእሳት ለተቃጠሉት፣ በሊብያ በአይሥስ ለታረዱትና በቀይ ባሕርና በሜዲትራኒያን ባሕር ለሰመጡት የወያኔን እንኳን ያህል ባይሆን፣ ጥቃቅን ልዩነቶችን አሽቀንጥረን አንድነት ፈጥረን ወያኔን ከጧቱ ከመሬት በታች ባለማዋላችን እኛም ከተጠያቂነት አናመልጥም።

ዛሬ በሃገራችን እንደቋያ እሳት ከዳር እስከዳር ተቀጣጥሎ ያለው ሕዝባዊ አመጽ ወያኔን ጉሮሮውን አንቆ በያዘበት ሰዓት እንኳን አንድነታችን አሥፈላጊና ጊዜ የማይሰጥ መሆኑን ለመረዳት እሱ እራሱ ጊዜ እየፈጀብን ነው። ወያኔ አንድ ባለመሆናችን የምናመቻችለትን መግቢያ ቀዳዳ እየፈለገና እያነፈነፈ እኛን ለመከፋፈል የሚያደርገውን ጥረት ከመቀጠሉም በላይ፣ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ አውጆ ወገናችንን በጅምላ ከመቼውም በበለጠ ሁኔታ በመጨፍጨፍ፣ በማሰርና በመግደል ላይ ነው። ሃገሪቷን በቀይ ቀለም ከፋፍሎ የነገ ተስፋዎቿን ወጣቶች ልጆቿን ዙሪያውን ከቦ በጥይት እየቆላቸው ነው። ይህንን ዓይነት ግፍ በጣሊያን ወረራ ጊዜ እንኳን እንዳልተፈፀመ እየተነገረ ነው። ወያኔን ይህን ሁሉ ግፍ እንዲፈፅም ያስቻለው ምዕራባውያን አጋሮቹ ያስታጠቁት መሳሪያ ብቻ ነው የምንል ከሆነ እራሳችንን እያታለልንና አሁንም ሃላፊነትን እየሸሸን ነው። ወያኔ በይበልጥ የሚተማመንበትና

በዋነኛነት የበጀው መሳሪያ የኛ መከፋፈልና አድነት ማጣት እንደሆነ ሳናመነታ ማመን አለብን። ወያኔ የተቃዋሚዎች እጥረት የለበትም። ሞልተናል። ስለአንድነት ማውራት ባይታክተንም አንድነትን በሥራ ማሳየቱ ለ25 ዓመታት ወጥተን ያልጨረስነው ቀጥ ያለ አቀበት ሆኖብናል። ዛሬ በመሃላችን ያለምንም ውጤት ስለአንድነት ጡዋትና ማታ ማውራቱ ራሱን የቻለ ባሕል ሆኗል። ይህ ጉንጭ አልፋ ባህል አክትሞ በተጨባጭ አንድነት በመሃላችን መኖር ያለበት ነገ ሳይሆን ዛሬ ነው እንላለን።

አንድነትን አስመልክቶ፣ባለፉት 25 ዓመታት አልፎ አልፎ ሙከራዎች ቢደረጉም ግባቸውን ሳይመቱ የውሃ ሽታ ሆነዋል። እንደማለዳ ጤዛ ተነዋል። ከወያኔ ጭቆና ባላነሰ ሁኔታ አንድነት ማጣታችን ወገናችንን እንደጎዳው ሊታመንበትና ሊሰመርበት ይገባል። ግን የመበታተን ጉም ተገፎ የአንድነት ብርሃን እንድንጎናፀፍና አገራችንንና ወገናችንን እንድንታደግ ዕድሉና ቁልፉ ያለው በእጃችን ነው። በ10/31/2016 በዋሺንግተን ዲሲ በአራት ድርጅቶች ጥምረት የተዋቀረው "የኢትዮጵያ አገራዊ ንቅናቄ" የሚያረጋግጥልን የህንኑ ነው። የአርበኞች ግንቦት 7 ለአንድነትና ዲሞክራሲ ንቅናቄ፣ የሲዳማ ብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ ንቅናቄ፣ የኦሮሞ ዲሞክራሲያዊ ግንባር እና የአፋር ሕዝባዊ ፓርቲ ልዩነቶቻቸውን ወደጎን በመተው ከዋናው ጠላት ወያኔ ላይ በማተኮር "የኢትዮጵያ አገራዊ ንቅናቄ"ን በመመሥረታቸው ጧትና ማታ ከወያኔ ጋር ትንቅንቅ ለያዘው ወገናችን የለገሱት ሞራልና ተስፋ በጣም የላቀ ለመሆኑ ጥርጥር የለንም። የኢትዮጵያውያን ሙስሊሞች ሰላማዊ ንቅናቄ ደጋፊዎች ሕብረት ጥምረቱን ለፈጠሩት የአራት ድርጅቶች መሪዎችና ከበስተጀርባ በመሆን ጥምረቱ እውን እንዲሆን ለለፉ አገር ወዳድ ወገኖቻችን አድናቆቱን እየገለፀ፣ ሌሎች ስብስቦች ጊዜ ሳያጠፉ ይህን አዲስ የተወለደ ድርጅት በመቀላቀል ለወገናቸው ፈጥነው እንዲደርሱ በጥብቅ ያሳስባል። የዛሬ መቶ ሃያ ዓመት ቅድመአያቶቻችን በአድዋ ላይ ጠላትን ድባቅ ያስገቡት "ዓመልህን በጉያህ፣ ሥንቅህን ባህያህ" የሚል መርህ አንግበው መሆኑን አንርሳ።

በአሁኑ ሰዓት በሃገራችን በመካሄድ ላይ ያለው ፀረ-ወያኔ ሕዝባዊ አመፅ የትግሉ አቅጣጫ ምን መልክ መያዝ እንዳለበትና ውጤቱ ምን መሆን እንዳለበት በማያሻማ መንገድ አመላክቶናል። ሕዝቡ የሚፈልገው የኢትዮጵያ ሉዓላዊነት ተጠብቆ ሥር-ነቀል የሥርዓት ለውጥና የዘረኛውን ወያኔን ላንዴና ለመጨረሻ ጊዜ መወገድ ስለሆነ በ"ኢትዮጵያ አገራዊ ንቅናቄ" ዣንጥላ ሥር የሚሰባሰቡ ሁሉ ሌላ የተለየ ዓላማ እንደማይኖራቸው የሚያጠያይቅ

አይመስለንም። ይህ አለኝታና ለወገን ደራሽ ድርጅት ወገኖቻችንን ተስፋ ብቻ ከመቀለብ አልፎ በገሃድ አንድ ሁለት ተብለው ሊቆጠሩ የሚችሉ ተጨባጭ ውጤቶችን ባስቸኳይ ማስመዝገብ መጀመር አለበትም እንላለን። አንድነት ሃይል ነውና።

የተባበረ የሕዝብ ክንድ ያሸንፋል!

በአላህ ፈቃድ እስከ ድል ደጃፍ እንንቀሳቀሳለን!!

አላሁ አክበር!

**የኢትዮጵያውያን ሙስሊሞች ሰላማዊ ንቅናቄ ደጋፊዎች ሕብረት**


4324 Georgia Avenue NW – Washington, DC 20011 uempmsg@gmail.com